በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት
የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Patriarchate Head Office
SUNDAY SCHOOL DEPARTMENT

ቁጥር 1090/153/18
Ref. No.

26/8 ቀን ፳፻ 18 ዓ/ም
Date 20

ለ...ሁሉም... ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት
...በያሉበት

ጉዳዩ፡- የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት የሥራ አመራር ምርጫ ማስፈጸሚያ ሰነድ ስለመላክ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ ከአጥቢያ እስከ መንበረ ፓትርያርክ የተናበበ አሠራርና ወጥ መዋቅራዊ አደረጃጀትን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲረዳ በተለይም በቃለ ዓዋዲ አንቀጽ 21/1 ድንጋጌ እና ቅዱስ ሲኖዶስ በ2006 ዓ.ም ባወጣው የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ውስጠ ደንብ መሠረት አንቀጽ 20 የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የጠቅላላ ጉባኤ ሥራና ኃላፊነት ላይ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ለዚሁ ማስፈጸሚያ በጠቅላላ ጉባኤው ተዘጋጅቶ በ2016 ዓ.ም ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ለሁሉም አህጉረ ስብከት መላኩ ይታወሳል፡፡ በተላከው የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ተቋማዊ አደረጃጀት የውስጥ ዝርዝር ማስፈጸሚያ ሰነድ የሚያስፈልጋቸው ተብለው ከተለዩ መካከል የሰንበት ትምህርት ቤቶች የሥራ አመራር ምርጫ ማስፈጸሚያ ሰነድ አንዱ ሲሆን በሁሉም አህጉረ ስብከት እስከ አጥቢያ ድረስ የሚተገበር ማስፈጸሚያ ሰነድ ተዘጋጅቶ እንዲላክ በተወሰነው መሠረት ሰነዱ ተዘጋጅቷል፡፡

በዚህም መሠረት ሰንበት ት/ቤቶች እንደ አመሠራረታቸው ካላቸው ልምድና አቅም ማለትም ከአደረጃጀት ግብዓት፣ ከአካባቢ እና የአገልግሎት የትኩረት አቅጣጫ አንጻር አቅማቸው የተለያየ በመሆኑ በአንድ ዓይነት መዋቅራዊ አደረጃጀት የሚጠበቀውን ተቋማዊ ተልእኮ ማሳካት ስለማይቻል ሰንበት ት/ቤቶች ደረጃ በደረጃ ወደ ከፍተኛው መዋቅራዊ አደረጃጀት እንዲመጡ አቅደው የሚሠሩበት አሠራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የሰንበት ት/ቤቶች ምርጫ በተናበበ ጊዜ እንዲሆንና አሳታፊነትን ታሳቢ በማድረግ የየመዋቅሩ የጠቅላላ ጉባኤ አመሠራረት፣ አደረጃጀትና የምርጫ አፈጻጸምን በተመለከተ በ13ኛው የመንበረ ፓትርያርክ የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ተዘጋጅቶ የቀረበው ይህ 20 ገጽ ማስፈጸሚያ ሰነድ መሠረት እንዲከናወንና ሰነዱ ለሁሉም መንበረ ጵጵስና፣ ወረዳ/ክ/ከተማ ሰ/ት/ቤቶች አንድነትና አጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች እንዲደርስ እያሳሰብን ለተግባራዊነቱ አስፈላጊውን የማስገንዘብና የድጋፍ ሥራ በየደረጃው ባለው የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት መዋቅር የሚከናወን መሆኑን ስንገልጽ በታላቅ አክብሮት ነው፡፡

"ወንድካብ ሰላመ በጎበ እግዚአብሔር"

E.O.T.C Patriarchate Head Office Sunday School department

መጋቤ ሐዲስ ጸጋ ወ/ትንሣኤ
መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት
የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ
መምሪያ ዋና ሓላፊ
Megabe Haddis Tsega W/Tensay (Rev)
E.O.T.C Patriarchate Head Office
Head of Sunday School Department

ግልባጭ
- ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤ/ክ ጽ/ቤት
- ለመምሪያው ሊቀ ጳጳስ

አዲስ አበባ
- ለ...ሁሉም... ሀገረ ስብከት ሰ/ት/ቤቶች አንድነት
...በያሉበት...

TEL. No. 251-1-56 57 32
251-1-56 72 79 55 00 98 55 00 99
251-1-58 07 69 – Ex 236/237
ፖ.ሣ.ቁ. 81286
አዲስ አበባ

## ማውጫ


1. መግቢያ ....3
2. የሰነዱ ዓላማ ....3
3. የመመሪያ ውወሰን ....3
4. የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ አመሠራርት፣ የመምረጥ መብትና አደረጃጃት ....4
5. በአጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች: ....4
5.1. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤት ጠቅላላ ጉባኤ መቋቋም ....4
5.2. የመደበኛ አባልነት ማዕቀፍ ....5
5.3. በሰንበት ት/ቤት ጠቅላላ ጉባኤነት የማይካተቱ ....6
5.4. የጠቅላላ ጉባኤው መደራጀት ....6
5.4.1. የጠቅላላ ጉባኤው የወል ድንጋጌዎች ....7
6. የወረዳ /ክፍለ ከተማሰንበትት/ቤቶችአንድነት ....8
6.1. የጠቅላላ ጉባኤው አመሠራረት ....8
6.2. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት ....8
6.3. የመመረጥ መብት እና ወሰን ....9
7. የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ ....9
7.1. ጠቅላላ ጉባኤ አመሠራረት ....9
7.2. የጠቅላላ ጉባኤው መደራጀት ....10
7.3. የመመረጥ መብት እና ወሰን ....10
8. የመንበረ ፓርትያርክ ሰንበትት/ቤቶችአንድነትጠቅላላጉባኤ ....11
5.1. የጠቅላላ ጉባኤው አመሠራረት ....11
8.2. የጠቅላላ ጉባኤው መደራጀት ....11
8.3. የመመረጥ መብት እና ወሰን ....12
9. የጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ጊዜ ....12
10. የሥራ አመራር የሥራ ዘመን ....12
11. የጠቅላላ ጉባኤያት ምርጫ የሚካሄዱባቸው ጊዜያት ....12
12. አዲሱን ማስፈጸሚያ ሰነድ አተገባበር አግባብ ....13
13. የሥራአመራርጉባኤአባላት የመመረጫ መሥፈርት ....14
14. የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት መዋቅር ተወካዮች አመራረጥ ....15
15. የመዋቅር ልዑካን እና ታዛቢዎች ....15
16. የአስመራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም ....16
16.1. የአስመራጭ ኮሚቴ መመረጫ መሥፈርት ....16
16.2. አስመራጭ ኮሚቴ ተግባርና ሓላፊነት ....16


በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
E.O.T.C Patriarchate Head Office Sunday School department

16.4. የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ....................18
16.5. የተመራጮች ሥራ ድልድል እና ቃለ መሐላ ....................18
16.6. ምርጫ በተመለከተ የሚነሱ ቅሬታዎች ....................18
16.7. በየደረጃው ያለው የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የሥራ አመራር አመራረጥ ....................18
16.8. ምርጫን ስለማሳወቅ ....................19
17. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ....................20

## 1. መግቢያ

ከአጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች እስከ መንበረ ፓትርያርክ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት የሥራ አመራር ምርጫ ማስፈጸሚ ሰነድ የተዘጋጀው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተተኪውን ትውልድ ተደራሽ ለማድረግ የተቋቋመው የሰንበት ት/ቤቶች መዋቅር በመዋቅራዊ መመሪያ ከ1974 ዓ.ም ጀምሮ በቃለ ዐዋዲው ተካቶ አገልግሎት በተደራጀት መልኩ ከተጀመረበት ጊዜያት በተለይም በቃለ ዓዋዲ አንቀጽ 21/1 ድንጋጌ እና በ2006 ዓ.ም ለሰ/ት/ቤቶች አንድነት በቅዱስ ሲኖዶስ በጸደቀው መመሪያ መሠረት እና ለዚሁ ማስፈጸሚያ በጠቅላላ ጉባኤው በ2016 ዓ.ም በወጣው የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ተቋማዊ አደረጃጀት የውስጥ ዝርዝር ማስፈጸሚያ ሰነድ መሠረት ለማስፈጸም የተዘጋጀ ነው፡፡

የሰንበት ት/ቤቶች መዋቅራዊ አደረጃጀት እንደ አመሠራረታቸው ካላቸው ልምድና አቅም አንጻር የተለያየ የአገልግሎት አሰጣጥ አቅምና አደረጃጀት ላይ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ከልምድ፣ ከአባላት ብዛት፣ ከአደረጃጀት ግብዓት፣ ከአካባቢ እና የአገልግሎት ትኩረት አንጻር የተለያየ አቅም ላይ በመሆናቸው በተመሳሳይ መዋቅራዊ አደረጃጀት ሥራዎችን ለመሥራት ውጤታማ ባለማድረጉ እና ከሚጠበቀው ተቋማዊ ተልዕኮ አንጻር ሰንበት ት/ቤቶች ደረጃ በደረጃ ወደ ከፍተኛው መዋቅራዊ አደረጃጀት እንዲመጡ አቅደው የሚሠሩ ሲሆን ወረዳ/ ከተማ ሰ/ት/ቤቶች አንድነት በመሥፈርቱ መሠረት በመመዘን እንዲደራጁ ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ ሲሆን መዋቅራዊ አደረጃጀቱ ውጤታማ እንዲሆንበመሥፈርት ተመዝነው በአቅማቸው ልክ እንዲዋቀሩ በማሰብ ሰንበት ት/ቤቶች በአራት የመዋቅር መደብ ተለይተው እንዲሠሩ አፈጻጸም ተዘጋጅቶለት ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

በዚህም መሠረት የተናበበ ተቋማዊ አወቃቀርን በመተግበር ሂደት ከሚጠበቁ ሥራዎች መካከል አንዱ የሆነ የሥራ አመራር ምርጫ ሥርዓት አፈጻጸም በሁሉም የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ጠቅላላ ጉባኤያት መሠረት አድርጎ የሚፈጸም እና አሳታፊ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ በየመዋቅሩ የጠቅላላ ጉባኤ አመሠራረት፣ መደራጀትና የመምረጥ መብትን አፈጻጸም በተመለከተ በዚህ ማስፈጸሚያ ሰነድ መሠረት እንዲከናወን ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

## 2. የሰነዱ ዓላማ

2.1. በ2016 ዓ.ም በወጣው የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ተቋማዊ አደረጃጀት የውስጥ ዝርዝር ማስፈጸሚያ ሰነድ መሠረት የተናበበ ተቋማዊ አወቃቀርን በሁሉም መዋቅር ተግባራዊ ለማድረግ፤

2.2. ሰንበት ትምህርት ቤቶች በአዲሱ መዋቅር ለማደራጀት፣ የመዋቅር ምድባቸውን እና አባላታቸውን ለይተው ሰንበት ት/ቤታቸውን የሚመሩ የክፍል አባላትን በማዋቀር ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት፤

2.3. ከአጥቢያ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ባለው መዋቅር የተናበበ እና ተመሳሳይ ጊዜ ሁሉምሰንበትትምህርትቤቶች በአዲሱ ተቋማዊአደረጃጀት መሠረት ሰንበት ት/ቤቶች እንዲደራጁ እና በአደረጃጀቱ ደረጃ መደብ መሠረት የአመራር ምርጫ አከናውነው እንዲያጠናቀቁ ለማድረግ፤

2.4. የሥራ አመራር ምርጫ ግልጽ በሆነ አሠራር በሁሉም መዋቅር በተናበበ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ፤

## 3. የመመሪያ ውወሰን

ይህ የሥራ አመራር ምርጫ ማስፈጸሚያ ሰነድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር የሚገኙ ሁሉም አድባራትና ገዳማት የሚገኙ ሰንበት ት/ቤቶች፣ የወረዳ/ ክፍለ ከተማ፣ መንበረ ጵጵስና እና መንበረፓትርያርክሰንበትትምህርትቤቶችአንድነት ጠቅላላ ጉባኤ በ2016 ዓ.ም በወጣው

E.O.T.C Patriarchate Head Office Sunday School department

የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ተቋማዊ አደረጃጀት የውስጥ ዝርዝር ማስፈጸሚያ ሰነድ አወቃቀር መሠረትበመደራጀት እና የሥራ አመራር አካላትን መርጠው እንዲያጠናቅቁ ለማድረግ በሁሉም ሰንበት ት/ቤቶችና የአንድነቱ መዋቅር ላይ ተፈጻሚለማድረግ ነው፡፡

## 4. የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ አመሠራረት፣ የመምረጥ መብትና አደረጃጃት

በቃለ ዓዋዲ አንቀጽ 21/1 ድንጋጌ እና በ2006 ዓ.ም ለሰ/ት/ቤቶች አንድነት በቅዱስ ሲኖዶስ በጸደቀው መመሪ ያመሠረተ ከመንበረ ፓትርያርክ ጠ/ቤተክህነት እስ ከአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ድረስ የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት መዋቅራዊ አሠራር ወጥ በሆነ መንገድ ለመፈጸም በ2016 ዓ.ም በወጣው የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ተቋማዊ አደረጃጀት የውስጥ ዝርዝር ማስፈጸሚያ ሰነድ መሠረት የተናበበ ተቋማዊ አወቃቀርን በመተግበር ሂደት ከሚጠበቁ ሥራዎች መካከል አንዱ የሆነ የሥራ አመራር ምርጫ ሥርዓት አፈጻጸም በሁሉም የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ጠቅላላ ጉባኤያት መሠረት አድርጎ የሚፈጸም ነው፡፡ በዚህም መሠረት በየመዋቅሩ የጠቅላላ ጉባኤ አመሠራረት፣ መደራጀትና የመምረጥ መብትን አፈጻጸም በተመለከተ በሚከተለው አግባብ ይሆናል፡፡

## 5. በአጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች፡

በውስጥ ዝርዝር ማስፈጸሚያ ሰነድ ምዕራፍ ሁለት አንቀጽ 2.1 የአጥቢያ ሰንበት ት/ቤት ጠቅላላ ጉባኤ መቋቋም እና 2.2. የጠቅላላ ጉባኤው መደራጀት በተመለከተ በተገለጸው መሠረት በሚከተለው አጋባብ ይሆናል፡፡፡

### 5.1. በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤት ጠቅላላ ጉባኤ መቋቋም

በቃለ ዓዋዲው አንቀጽ 12/መ/፣ 17/17 ድንጋጌ እና በ2006 ዓ.ም ለሰ/ት/ቤቶች አንድነት በቅዱስ ሲኖዶስ በጸደቀው መመሪያ መሠረት ከመንበረ ፓትርያርክ ጠ/ቤተ ክህነት እስከ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ድረስ የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የሚቋቋም ሲሆን በዚህም መሠረት በአጥቢያ ደረጃ፡-

በቃለ አዋዲው አንቀጽ 12/መ/እና 17/17/ ድንጋጌ መሠረት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት ይቋቋማል፡፡

5.1.1. በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕጻናት፣ ታዳጊዎች፣ ወጣቶችና ጎልማሶችን የተመለከተ ማዕቀፍ ይዞ የሚቋቋመው ሰንበት ት/ቤት አንድ ብቻ ነው፡፡

5.1.2. የአጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች የሚጠሩበት ስያሜ በዋነኛነት በቤተ ክርስቲያኑ ስም ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ለአገልግሎት የሚያበረታታ እና መታሰቢያ የሚሆን የተለያየ ስያሜ ሊኖራቸው ይችላል፡፡

5.1.3. የአጥቢያ ሰንበት ት/ቤት አገልግሎት እና የጠቅላላ ጉባኤው መደራጀት

5.1.4. የአጥቢያ ሰንበት ት/ቤት በአንድ አጥቢያ ላይ በአባላቱ ጠቅላላ ጉባኤ የሚቋቋም፤ በአጥቢያው ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች በሙሉ ልጆቻቸውን ወደ አጥቢያ ሰንበት ት/ቤት በማምጣት የሚመሠረት፤ ሕጻናት፣ታዳጊዎች፣ ወጣቶች እና ጎልማሶች መንፈሳዊ ትምህርት የሚያገኙበት እና የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በመማርም በሕይወታቸው ተጠቃሚ የሚሆኑበት ነው፡፡

5.1.5. የአጥቢያ ሰንበት ት/ቤት ጠቅላላ ጉባኤ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የወጣቶችና የጎልማሶች የአባልነት ማረጋገጫ በመያዝ በአጥቢያው ሙሉ እውቅና ይደራጃል፡፡

5.1.6. ሰንበት ት/ቤቱም በጠቅላላ ጉባኤ የሚመራ ሲሆን ይህ ጠቅላላ ጉባኤ በሰንበት ት/ቤቱ በአባልነት ላገለገለ እና እያገለገለ ላለው ኹሉ በሚዘረጋለት የማዕቀፍ መርሐ ግብር ላይ እስከተሳተፈ ድረስ በእኩልነት የአባልነት መብት የሚሰጥ፣ በአመራር ድርሻም እንደአስፈላጊነቱ ባለ መብት የሚኮንበት ሆኖ፡-

- ✓ መደበኛ አባላት ማዕቀፍ
- ✓ የልዩ መደበኛ አባላት ማዕቀፍ
- ✓ የክብር አባላት ማዕቀፍ በሚሉ የሰንበት ት/ቤቱ የጠቅላላ ጉባዔ አባልነት መገለጫዎች የሚታወቅ ጠቅላላ ጉባዔ ይሆናል፡፡ ስለሆነም በጠቅላላ ጉባኤነት መንፈስ ሰንበት ት/ቤቱን የመምራት፣ የመቆጣጠር እና አቋም የመግለጥ መብቱ ሙሉ በሙሉ የተጠበቀ ነው፡፡

5.2. የመደበኛ አባልነት ማዕቀፍ

ይህ የመደበኛ አባላት ማዕቀፍ

5.2.1. በሰንበት ት/ቤቱ አባልነት በሰንበት ት/ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት መሠረት በተዘረጋ ክፍሎች የሚማሩ ሆነው እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆነና በማገልገል ላይ ያሉ፡፡

5.2.2. በሰንበት ት/ቤቱ አባልነት በሰንበት ት/ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት መሠረት በተዘረጋ ክፍሎች የሚማሩ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆነ በህጻናትና በታዳጊዎች መርሐ ግብር እያገለገሉ የሰንበት ት/ቤቱ መደበኛ አባላት ሆነው በጠቅላላ ጉባኤ መምረጥ መመረጥ ውስጥ የማይሳተፉ መደበኛ አባላት ናቸው ፡፡

5.2.3. ሰንበት ት/ቤቱ በቅበላ መሥፈርት ጥሪ አድርጎ ለሚቀበላቸው ፣ለሚያሰለጥናቸው እና አባል ለሚያደርጋቸው፤

5.2.4. በሰንበት ት/ቤቱ በሚዘረጋቸው የአገልግሎት ክፍሎች ውስጥ ለሚሳተፉ፤

5.2.5. ከሌሎች የመኖሪያ ቦታዎች በታወቀ ምክንያት ወደዚህ አጥቢያ ለመዛወራቸው የሸኚ ደብዳቤ ማቅረብ ለሚችሉ፤

5.2.6. የሰንበት ት/ቤቱ መደበኛ አገልግሎት እንዲከናወንና ሰንበት ት/ቤቱ የሚጠበቅበትን የሥራ ድርሻ እንዲወጣ በጉልበት፣በእውቀት፣በገንዘብ ድጋፍ ለሚያደርጉ በአጠቃላይ በወጣትነታቸው ወራት በንቃት እና በትጋት ዕለት ዕለት በሰንበት ት/ቤቱ ሥራ ላይ ተሳታፊ ለሚሆኑ፤

5.2.7. በሰንበት ት/ቤቱ የቅበላ አቅም እና መሥፈርት የአባልነት ቅጽ የፈረሙ፤

5.2.8. የልዩ መደበኛ አባላት ማዕቀፍ

በዚህ ማዕቀፍ የሚጠሩ የማዕቀፉ አባላት

5.2.8.1. በሰንበት ት/ቤቱ መደበኛ የወጣቶች መርሐ ግብር ላይ ቀድሞ በነበራቸው የአገልግሎት ጊዜ በዘመናቸው ያገለገሉ እና የሚያገለግሉ፤ በተለያዩ ጊዜያት የአባልነት ግዴታቸውን የተወጡ፤

5.2.8.2. በአስተባባሪነት ፣ በመምህርነት ፣ በንዑስ አስፈጻሚነት፣ በአስፈጻሚነት ፣በሥራ አመራርነት ፣ በአማካሪነት፣ በሰበካ ጉባኤ ፣ በልማት፣ በስብከተ ወንጌል እና በተለያየ አቻ የበላይና የበታች ጽ/ቤት የሰንበት ት/ቤት ተጠሪነት ያገለገሉ እና በማገልገል ላይ ያሉ፤

5.2.8.3. በጊዜ እና በቦታ አለመመቸት በመደበኛው መርሐ ግበር ላይ ለመገኘት የማይችሉ፤

5.2.8.4. በአባልነታቸው ወቅታዊ እንቅስቃሴ በማካሄድ ድርሻቸውን መወጣት የሚችሉ፤

5.2.8.5. በአባልነታቸው በጉልበት በገንዘብ እና በእውቀት ሰንበት ት/ቤቱን የሚረዱ፤

5.2.8.6. በቀድሞ የሰንበት ት/ቤት ቆይታቸው የሰንበት ት/ቤቱን የአባልነት ቅጽ የፈረሙ ፤

5.2.8.7. ቀድሞ በሰንበት ት/ቤቱ የመደበኛ አባልነት ቆይታቸው ከ20 ዓመት በላይ ያስቆጠሩ፤

5.2.8.8. አሁንም ባለው የሰንበት ት/ቤት የአባልነት ቅድመ ሁኔታ ቅድሚያውን ለሰንበት ትምህርት ቤቱ የሚሰጡ፤

5.2.8.9. በሚዘረጋላቸው መርሐ ግብር አገልግሎት መስጠት እና መገልገል ለመቻላቸው ማረጋገጥ የቻሉ እና የሚችሉ ሲሆኑ በየትኛውም መልኩ ዕለት ዕለት የሚጠበቅባቸውን ለመወጣት እስከ ቻሉ ድረስ ከምሥረታው ጀምሮ ያሉ አባላት ለመሆን ይችላሉ።

5.2.8.10. በዚህ ማዕቀፍ እንደ ሰንበት ት/ቤቱ ልምድ እና ነባራዊ ሁኔታ ልዩ ልዩ ጉባኤያት ሊኖሩ ይችላሉ ። ለምሳሌ እንደ ጉባኤ አርድዕት ዓይነት ሊቋቋም ይችላል።

5.2.9. የክብር አባልነት ማዕቀፍ

ይህ ማዕቀፍ

5.2.9.1. በሰንበት ት/ቤቱ የመርሐ ግብር አወቃቀር በየትኛውም እርከን ያለፉ እና ያላለፉ፤

5.2.9.2. ከመደበኛው እስከ ልዩ መደበኛ አባልነት ባለው ጀምሮ ባለ ማዕቀፍ የትምህርት መርሐግብር ለመካተት የማይችሉ እና የማይካተቱ፤

5.2.9.3. በአጥቢያውም ሆነ በሌላ አጥቢያ የኖሩ፣ የሚኖሩ ፣ ለሰንበት ት/ቤቱ በገንዘብ ፣ በጊዜ በጉልበትና በመሳሰሉት አስተዋጽዖ ያበረከቱ ፤

5.2.9.4. ዘወትር የሰንበት ት/ቤቱ ህልውና የአባላቱ ብስለት፣ የመማር ማስተማሩ ሒደት ጥንካሬ፣ የሚያሳስባቸው

5.2.9.5. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች የሆኑ ጳጳሳት፣ መምህራን፣ ካህናት፣ዲያቆናት እና ምእመናን ሲሆኑ ሰንበት ት/ቤቱ ለእነዚህ አባላት በሚያዘጋጀው በየትኛውም ዓይነት ጥሪ የሚገኙ የሚመክሩ፣ የሚያስተምሩ፣ በበጎ አድራጎት ለሚራዱ እና ሰንበት ት/ቤቱ ለሚሰጣቸው የክብር አባልነት ዕውቅና ፍላጎቱ ያላቸው። በጠቅላላ ጉባኤ መገኘት የሚችሉ ቢሆንም የመምረጥና የመመረጥ መብት ግን አይኖራቸውም።

5.3. በሰንበት ት/ቤት ጠቅላላ ጉባኤነት የማይካተቱ

ሀ. ወደ ሰንበት ት/ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት ለመግባት የቅድመ ዝግጅት ኮርስ በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች

ለ. በአጥቢያው ሰንበት ት/ቤት አስተባባሪነት የሚከናወን የግቢ ጉባኤያት ፤

ሐ. የካህናት የንስሓ ልጆች ጉባኤ፤

መ. በልዩ ልዩ ሁኔታ በአጥቢያው ሰንበት ት/ቤት ስር የሚከናወኑ የወጣቶች ፣ የጎልማሶች ፣ የጽዋ ማኅበራት ትምህርት መርሐ ግብር ማስፈጸሚያ ጉባኤዎች <u>በሙሉ የጠቅላላ ጉባኤነት አቋም በሙሉም ሆነ በከፊል አይኖራቸውም</u>።

በአጥቢያ ሰንበት ት/ቤት የሚዘረጉ የትምህርት አገልግሎት መርሐ ግብሮች በመጨረሻ አፈጻጸማቸው የመርሐ ግብሩ አባላት ወደ ሰንበት ት/ቤቱ መደበኛ መርሐ ግብር በፈቃዳቸው እንዲቀላቀሉ የታለመ ስለሆነ የሚሰጠውን ልዩ መርሐ ግብር ሲያጠናቅቁ ሰንበት ት/ቤቱ በሚያስቀምጠው መሥፈርት መሠረት ማሟላት ከቻሉ ወደ ሰንበት ት/ቤቱ ይጠቃለላሉ። ያን ጊዜ የመደበኛ አባልነት ቅጽ ፈርመው የጠቅላላ ጉባኤው መብት እና ግዴታ ይፈጸምላቸዋል።

5.4. የጠቅላላ ጉባኤው መደራጀት

ጠቅላላ ጉባኤው ከዚህ ቀደም በነበረበት መልኩ የሚቀጥልበት እና አደረጃጀቱም ሲኖዶሳዊ / በቅዱስ ሲኖዶስ በተሰጠው እና በሚሰጡ የአደረጃጀት መዋቅር / መሠረትነት ያለው ሆኖ በሌላ መልኩ በበጎ ፍቃድ ለመንፈሳዊ በረከት በሁሉም ጊዜና ሰዓት ሰንበት ት/ቤቱን የተመለከተ ውሳኔ ለመስጠት የመጨረሻ የሆነ ሥልጣን ያለው ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል ።

በሁሉም አጥቢያዎች በሚደረግ ግንዛቤ ማስጨበጫ መሠረት ማዕቀፎችን ማስረጽ ቅድሚያ የሚሰጠው ይሆናል። በዚህ መሠረት ለዚህ የማዕቀፍ ማስፈጸሚያ የሚዘጋጁ የጥሪ፣ የምዝገባ እና የምሥረታ መርሐ ግብሮች እንዲኖሩ ማድረግ የአጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች ግዴታ ይሆናል።

E.O.T.C Patriarchate Head Office Sunday School department

ሁሉም ማዕቀፎች ከሰረጹ በኋላ ከላይ ከተዘረዘሩት ሦስት ማዕቀፎች ውስጥ የሰንበት ት/ቤቱን ጠቅላላ ጉባኤ አቋም በመጠከልና በመምራት የተሻለ እንቅስቃሴ ሊያደርጉ የሚችሉ እና በተለይም በዚህ ዘመን የተሻለ አደረጃጀት ባላቸው ሰንበት ት/ቤቶች ላይ ለማየት እንደሚቻለው በምክንያታዊነት የሚቀመጡት

ሀ. የመደበኛ አባላት እና

ለ. የልዩ መደበኛ አባላት ይሆናሉ። በዚህ መሠረት ጠቅላላ ጉባኤው የሰንበት ት/ቤቱን የሥራ አመራሮችና የአፈጻጸም ቁጥጥርና ክትትል ጉባኤን ይሰይማል። የሥራ አመራር ጉባኤው ከመካከሉ ለሰብሳቢነት የሚመርጠው አባል የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል።

5.4.1. **የጠቅላላ ጉባኤው የወል ድንጋጌዎች**

5.4.1.1. የሰንበት ት/ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤም ሰንበት ት/ቤቱ በሕግ የተመሠረተበት ዘመንን ተንተርሶ እና በየዓመቱ ለሁለት ጊዜያት የሚከናወን ጠቅላላ ጉባኤ እንደሚኖር ታስቦ የ________ ዓመት 1ኛ ወይም 2ኛ መደበኛ ጉባኤ በሚል መጠሪያ ይከናወናል።

5.4.1.2. የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎቹም የ________ ዓመት 1ኛ ወይም 2ኛ መደበኛ ጉባኤ ውሳኔ ይባላሉ። በልዩ ልዩ ሁኔታዎች ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤም በዚህ ዓይነት የሚጠራ እና የሚካሄድ ይሆናል።

5.4.1.3. ጠቅላላ ጉባኤውን መሠረት ያደረገ የአስተዳደር ፣ የአፈጻጸምና የአመራር ዝርዝርም ወጥነት ባለው መልኩ በሁሉም አጥቢያዎች ወጥ ሆኖ ከማደራጃ መምሪያው የሚወጣ እና በሥራ ላይ የሚውል ይሆናል።

5.4.1.4. አጥቢያ ሰንበት ት/ቤት ከግንቦት እስከ ሀምሌ መጨረሻ ፤ወረዳ ክፍለ ከተማ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት መስከረም እና ጥቅምት መንበረ ጵጵስና ሀገረስብከት ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ታህሳስ፤ መንበረ ፓትርያሪክ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት በባዐለ ጰራቅሊጦስ እለት ግንቦት ወይም ሰኔ ጠቅላላ ጉበኤምርጫ የሚፈጽሙ ይሆናል

5.4.1.5. በሰንበት ት/ቤቶች ጠቅላላ ጉባኤያት ላይ በየደረጃው ካለው የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ተወካይ ልዑካን ይሳተፋሉ።

5.4.1.6. እያንዳንዱ አጥቢያ ሰንበት ት/ቤት ለወረዳ ወይም ክ/ከተማ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት በመሥፈርቱ መሠረት የሰንበት ት/ቤቱን ሰብሳቢና ሁለት ልምድ ያለው/ት/ አባል ይመድባሉ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ተጨማሪ አባላትን ለወረዳ/ክፍለ ከተማ/፤ ለመንበረ ጵጵስና ወይም መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተክህነት ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት በልምዳቸው ለአመራርነት እና ለክፍል ኃላፊነት ከታጩ ሰንበት ት/ቤቱ ውክልናውን ዕውቅና ሰጥቶ ለጠቅላላ ጉባኤ አባልነት ይልካል ።

5.4.1.7. በመዋቅር መደብ አንድ ላይ የሚገኙ አጥቢያዎች 11 ሥራ አመራር ጉባኤ ሲኖራቸው የሥራ አመራር ጉባኤው ሰብሳቢ ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ዋና ጸሐፊ እንዲሁም ልዩ ልዩ በቊጥር 8 / ስምንት/ የሆኑ የሥራ ማስተባበሪያዎች ይኖሩታል። የሥራ አስፈጻሚ ጉባኤው ሰብሳቢ በቅጥር በማይሆንበት ጊዜ ሥራ አመራሩ ቁጥር 12 ሆኖ የሥራ አስፈጻሚ ጉባኤው ቁጥር 11 ሲሆን በሰብሳቢነት ዋና ሥራ አስፈጻሚው ከሥራ አመራር የሚመደብ ሲሆን ለ9 ክፍሎችና አንድ ምክትል ሥራ አስፈጻሚ 10 አባላት በአመራሩ ተመርጠው ይመደባሉ።

5.4.1.8. በመዋቅር መደብ ሁለት ላይ የሚገኙ አጥቢያዎች 9 ሥራ አመራር ጉባኤ ሲኖራቸው የሥራ አመራር ጉባኤው ሰብሳቢ እና ዋና ጸሐፊ እንዲሁም ልዩ ልዩ በቊጥር 7 / ሰባት/ የሆኑ የሥራ ማስተባበሪያዎች ሲኖሩት የሥራ ~~አስፈጻሚ~~ ጉባኤው ቁጥር 9 ሲሆን በሰብሳቢነት ዋና ሥራ

አስፈጻሚው ከሥራ አመራር የሚመደብ ሲሆን ለ7 ክፍሎችና አንድ ምክትል ሥራ አስፈጻሚ 8 አባላት በአመራሩ ተመርጠው ይመደባሉ፡፡

5.4.1.9. በመዋቅር መደብ ሦስት ላይ የሚገኙ አጥቢያዎች 9 ሥራ አመራር ጉባኤ ሲኖራቸው የሥራ አመራር ጉባኤው ሰብሳቢ እና ዋና ጸሐፊ እንዲሁም ልዩ ልዩ በቊጥር 7 / ሰባት/ የሆኑ የሥራ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ ሥራ አስፈጻሚ ጉባኤ አይኖራቸውም፡፡

5.4.1.10. በመዋቅር መደብ ዐራት ላይ የሚገኙ አጥቢያዎች 7 ሥራ አመራር ጉባኤ ሲኖራቸው የሥራ አመራር ጉባኤው ሰብሳቢ እና ዋና ጸሐፊ እንዲሁም ልዩ ልዩ በቊጥር 5 / አምስት/ የሆኑ የሥራ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ ሥራ አስፈጻሚ ጉባኤ አይኖራቸውም፡፡

## 6. የወረዳ /ክፍለ ከተማሰንበትት/ቤቶችአንድነት

### 6.1. የጠቅላላ ጉባኤው አመሠራረት

በወረዳ ቤተ ክህነቱ ሥር የሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶች የወረዳው /ክፍለ ከተማው/ ቤተ ክህነት ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ናቸው፡፡ ሁሉም ወረዳ/ክፍለ ከተማ/ ሰንበት ት/ቤቶች በአመራሮቻቸው አማካኝነት ይወከላሉ፡፡

6.1.1. የወረዳ /ክፍለ ከተማ/ ቤተ ክህነት ሰንበት ት/ቤት ክፍል ሓላፊ እና የክፍሉ ሠራተኞች

6.1.2. የወረዳው /ክፍለ ከተማው/ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ሥራ አመራር አባላት፤

6.1.3. የወረዳው /ክፍለ ከተማው/ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አመራሮች፤

6.1.4. ከአጥቢያ ሰንበት ት/ቤት የሚወክል የአንድነቱ ሁለት ተወካይ (ሰብሳቢው እና በአጥቢያው የአንድነቱ ተወካዮች) እና በልዩ ሁኔታ ከአጥቢያ ሰንበት ት/ቤት በልምዳቸው ወደ ጠቅላላ ጉባኤ የሚጋበዙ አባላት፤

6.1.5. የመንበረ ጵጵስና ሰንበት ት/ቤቶች አንደነት ተወካይ ልዑካን፤

6.1.6. በወረዳው /ክፍለ ከተማው/ የክፍል አገልጋዮች፣ አፈጻጸም አማካሪዎች፣ ልምድ ያላቸው አባላት እና በሥሩ ካሉ ሰንበት ት/ቤቶች ውስጥ በአመራር ብስለት ፣ በመንፈሳዊ እና ዓለማዊ የትምህርት ዝግጅት የተሻለ ደረጃ ያላቸው አንጋፋ አባላት ሰንበት ት/ቤቶቻቸው በሚሰጡት ማረጋገጫ ከክፍለ ከተማው አመራሩ በሚሰጥ ኮታ መሠረተ ቊጥራቸው ተወስኖ የጠቅላላ ጉባኤው አባላት ይሆናሉ፡፡

6.1.7. እንደየአህጉረ ስብከቱ ተጨባጭ ሁኔታ አወቃቀራቸው ወረዳ ሳይኖር ከሀገረ ስብከት ቀጥታ ወደ አጥቢያ በሚሆንበት ጊዜ እና በውጭ አህጉረ ስብከት አወቃቀር የጠቅላላ ጉባኤነት መሥፈርቱ ማደራጃ መምሪያው በሚያዘጋጀው ዝርዝር የአፈጻጸም ስልት መሠረት ይሆናል፡፡

### 6.2. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

6.2.1. የጠቅላላጉባኤውሰብሳቢየወረዳ / ክፍለከተማ / የሰንበትት/ቤትክፍልሓላፊ እና የወረዳ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ተቀዳሚ ምክትል ሰብሳቢይሆናሉ፡፡

6.2.2. የወረዳ / ክፍለ ከተማ / የሰንበት ት/ቤት ክፍል ሓላፊ እና የአንድነቱ ተቀዳሚ ምክትል ሰብሳቢ በሌሉበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው እና ጸሐፊው የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

6.2.3. የአንድነቱ ምክትል ሰብሳቢ እና የአንድነቱ ዋና ጸሐፊ በጋራ በመሆን የጠቅላላ ጉባኤው ዋና ጸሐፊዎች ይሆናሉ ፡፡

6.2.4. የወረዳ / ክፍለከተማ/ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ የሰብሰባ ጊዜው በዓመት ሦስት ጊዜት ሆኖ የሥራ ዘመኑን በየአራት ወሩ የሚከናወን ይሆናል፡፡ አስቸኳይ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ልዩ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

6.2.5. የወረዳ / ክፍለ ከተማ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት አባላት ከ ¼ በላይ በሚሆን ጥያቄ ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

6.2.6. ከላይ በቊጥር 5.1. የተገለጠውን ለማካሄድ ከጠቅላላ ጉባዔ አባላት መካከል 51 % / ከመቶ ግማሽ እጅ በላይ / ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፣ ይህ ሳይሟላ ቀርቶ ሁለተኛ ጥሪ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በአግባቡ ለአባላት መድረሱ ሲረጋገጥ በተገኙት አባላት በጥሪው ላይ በተገለጸው አጀንዳ ላይ ብቻ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

6.2.7. የጉባኤው ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባ በተገኙ አባላት ድምፅ ብልጫ ወይም በምልዓተ ጉባኤው ሙሉ ስምምነት ሆኖ እኩል ድምፅ ሲኖር ሰብሳቢው የደገፈው ኀሳብ ተፈጻሚ ይሆናል።

6.2.8. በስብሰባና ውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት ላይ ከተጠቀሱት ውጭ የሆነ ነገር ቢገጥም ጥቅምት 14 ቀን 2006 ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ በወጣው የሰንበት ት/ቤቶች የውስጥ መመሪያ እና በሚዘጋጀው የጠቅላላ ጉባኤ አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል።

### 6.3. የመመረጥ መብት እና ወሰን

6.3.1. ሁሉም የጠቅላላ ጉባኤው አባላት በጠቅላላ ጉባኤነት በእኩል ድምፅ የመስጠት መብት ሲኖራቸው በሥራ አመራር እና በአፈጻጸም ቊጥጥርና ክትትልነት ለመመረጥ የሚችሉት ከአጥቢያ ሰንበት ት/ቤት ለአንድነቱ የሥራ ዘመናት በቋሚነት የሚወከል የአንድነቱ ተወካይ አባል እና በምስክርነት የተደገፈ ያፈጻጸም ጥንካሬ ያላቸው ስለመሆኑ ከአንድነቱ እንዲሁም ከአጥቢያ ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የሰንበት ት/ቤት አባላት ብቻ ናቸው።

6.3.2. ጠቅላላ ጉባኤው የሚመርጠው በቊጥር 11 / ዐሥራ አንድ / የሆኑ የወረዳው /ክፍለ ከተማው/ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የሥራ አመራር እና በቊጥር ከ2 እስከ 5 / ከሁለት እስከ አምስት / የሆኑ የአፈጻጸም ቊጥጥርና ክትትል ጉባኤ አባላት ይወከላል ።

6.3.3. ከተመረጡት የሥራ አመራር ጉባኤው አባላት መካከልም አንድ ተቀዳሚ ምክትል ሰብሳቢ፣አንድ ምክትል ሰብሳቢና አንድ ዋና ጸሐፊ የሚሰየም ሲሆን የተቀሩት አባላት የየክፍል ሓላፊዎች እና አባላት ይሆናሉ።

6.3.4. የወረዳው /ክፍለከ ተማው/ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የሥራ አመራር እና የክትትልና ቊጥጥር ጉባኤ አባላት የአንድነቱ ከፍተኛ የአስተዳደር ሓላፊዎች ሆነው በመናበብ አገልግሎቱን ይመራሉ።

## 7. የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ

### 7.1. ጠቅላላ ጉባኤ አመሠራረት

በመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስበከቱ ሥር የሚገኙ የወረዳ /የክፍለ ከተማ/ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ኹሉ የሀገረ ስብከቱ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ናቸው። ኹሉም የወረዳ /የክፍለ ከተማ/ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት በአመራሮቻቸው አማካኝነት ይወከላሉ። በዚህም መሠረት የጠቅላላ ጉባኤው አባላት፡-

7.1.1. የሀገረ ስብከቱ ሰንበት ት/ቤቶች ዋና ክፍል ሓላፊ እና የዋና ክፍሉ ሠራተኞች

7.1.2. የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ሥራ አመራር ፣ ሥራ አስፈጻሚ እና የንዑስ ክፍል አባላት፤

7.1.3. በሀገረ ስብከቱ ሥር ያሉ የወረዳዎች /የክፍላተ ከተሞች/ የሰ/ት/ቤት ክፍል ሓላፊዎችና የአንድነት የአመራር አካላት፣

7.1.4. የሀገረ ስብከቱ መቀመጫ ከተማ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት አባላት እና ለአንድነቱ የተወከሉ አባላት፣

7.1.5. የመንበረ ፓትርያርክ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ተወካዮ ዐካን፣



E.O.T.C Patriarchate Head Office Sunday School department

7.1.6. በሀገረ ስብከቱ ባሉ ሰንበት ት/ቤቶች ውስጥ በአመራር ብስለት ፣ በመንፈሳዊ እና ዓለማዊ የትምህርት ዝግጅት የተሻለ ደረጃ ያላቸው አንጋፋ አባላት ሰንበት ት/ቤቶቻቸው በሚሰጡት ማረጋገጫ መሠረት የሀገረ ስብከቱ አንድነት አመራሩ በሚሰጥ ኮታ መሠረት ቊጥራቸው ተወስኖ የጠቅላላ ጉባኤው አባላት ይሆናሉ፡፡

7.1.7. ከመደበኛው አደረጃጀት ውጪ በቀጥታ ለሀገረ ስብከቱ ተጠሪ የሆኑ የሰንበት ት/ቤት አደረጃጀቶች ቢኖሩ እንደየ ተጨባጭ ሁኔታቸው የጠቅላላ ጉባኤ አባልነት መሥፈርቱ ማደራጃ መምሪያው በሚያዘጋጀው ዝርዝር የአፈጻጸም ስልት መሠረት ይሆናል፡፡

## 7.2. የጠቅላላ ጉባኤው መደራጀት

ከላይ በቊጥር 7.1 በተዘረዘሩት በጋራ በመሆን የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት የሰንበት ት/ቤቶች አንድነትን ጠቅላላ ጉባኤ ይመሠርታሉ፡፡

7.2.1. የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሀገረ ስብከቱ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ ዋና ክፍል ሓላፊ እና የሰ/ት/ቤቶች አንድነት ተቀዳሚ ም/ሰብሳቢ ይሆናሉ፡፡

7.2.2. ሁሉም የጠቅላላ ጉባኤው አባላት በጠቅላላ ጉባኤነት በእኩል ድምፅ የመስጠት መብት ሲኖራቸው በሥራ አመራር እና በአፈጻጸም ቊጥጥርና ክትትልነት ለመመረጥ የሚችሉት ከአጥቢያ ሰንበት ት/ቤት ለአንድነቱ የሥራ ዘመናት የሚወክል የአንድነቱ ተወካይ አባል እና ያፈጻጸም ጥንካሬ ያላቸው ስለመሆኑ ከአንድነቱ እንዲሁም ከአጥቢያ ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የሰንበት ት/ቤት አባላት ብቻ ናቸው፡፡

7.2.3. ጠቅላላ ጉባኤው የሚመርጠው የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ሥራ አመራር ቊጥር eንደ ሰንበት ት/ቤቱ አንድነት መደብ ከ7/ሰባት/ እስከ 11 / ዐሥራ አንድ / የሆነ የሀገረ ስብከት የአፈጻጸም ክትትል ጉባኤ ቊጥሩ ከ2 እስከ 5 / ከሁለት እስከ አምስት / ይሆናል ፡፡

7.2.4. ከተመረጡት የሥራ አመራር ጉባኤው አባላት መካከልም አንድ ተቀዳሚ ምክትል ሰብሳቢ ፣ አንድ ምክትል ሰብሳቢና አንድ ዋና ጸሐፊ የሚሰየም ሲሆን የተቀሩት አባላት የየማስተባበርያ ሓላፊዎች እና አባላት ይሆናሉ፡

7.2.5. በቊጥጥርና አፈጻጸም ክትትል ጉባኤ አባላት መካከልም አንድ ሰብሳቢ ፣ አንድ አንድ ጸሐፊ የሚሰየም ሲሆን የተቀሩት የጉባኤው አባላት ይሆናሉ፡፡

## 7.3. የመመረጥ መብት እና ወሰን

7.3.1. ሁሉም የጠቅላላ ጉባኤው አባላት በጠቅላላ ጉባኤነት በእኩል ድምፅ የመስጠት መብት ሲኖራቸው በሥራ አመራር እና በአፈጻጸም ክትትልነት ለመመረጥ የሚችሉት /

7.3.1.1. ከወረዳ/ ክ/ከተማ የሰንበት ት/ቤቶች አንድነትአንድ የሥራ ዘመን ለመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰ/ት/ቤቶች አንድነት በቋሚነት ከተመረጡ አባላት ሲሆን ለክ/ሀገር ወረዳዎች በጣም የተራራቁ በመሆናቸው ከመንበረ ጵጵስና መቀመጫ እና ዙርያ ወረዳዎች አጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች ይሆናል

7.3.1.2. በአንድነቱ ጥያቄ መሠረት ከመንበረ ጵጵስናመቀመጫ ከተማ ከሚገኙ በአጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች የተረጋገጠላቸው አንጋፋ እና ጠንካራ የሚባሉ አገልጋይ፣ ምሁራንና ባለሙያዎች የሰንበት ት/ቤት አባላት

7.3.1.3. የአፈጻጸም ጥንካሬ ያላቸው ስለመሆኑ ከአንድነቱ እንዲሁም ከአጥቢያ ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የሰንበት ት/ቤት አባላት ብቻ ይሆናሉ፡፡

**8. የመንበረ ፓርትያርክ ሰንበትት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ**

**8.1. የጠቅላላ ጉባኤው   አመሠራረት**

8.1.1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤቶች መዋቅራዊ አደረጃጀቶች ኹሉ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ናቸው፡፡

8.1.2. በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥር ያሉ የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነቶች ኹሉ በአመራሮቻቸው አማካኝነት ይወከላሉ፡፡ በዚህም መሠረት፡-

8.1.2.1. የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሓላፊ፣ የመምሪያው የክፍል ሓላፊዎች እና ሠራተኞች፤

8.1.2.2. የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ሥራ አመራር፣ ሥራ አስፈጻሚ አባላት፤ ልዩ ልዩ የሥራ ልኡካን እና ፖሊሲና ስትራቴጂ ጉዳይ አማካሪዎች፤

8.1.2.3. የአህጉረ ስብከት ሰንበት ት/ቤት ዋና ክፍል ሓላፊዎችና የሀገረ ስብከት ሰ/ት/ቤቶች አንድነት ጽ/ቤቶች፤

8.1.2.4. የክ/ከተማ ወይም ወረዳ ቤተ ክህነት ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት አመራር አንድ ተወካይ፤

8.1.2.5. ለአዲስ አበባ እና አካባቢው አሕጉረ ስብከት ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት አመራሮች ፤

8.1.2.6. በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት እና በዙርያ አሕጉረ ስብከት ልምድ ያላቸው እና በተለያየ ኮሚቴ የተሳተፉ አባላት የጠቅላላ ጉባኤው አባል እንዲሆኑ በሚወጣው ዝርዝር አፈጻጸም መመሪያ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

8.1.3. ከመደበኛው አደረጃጀት ውጪ በቀጥታ በተለያዩ ክፍለ ዓለማት የሚፈጠሩ የሰንበት ት/ቤት አደረጃጀቶች ቢኖሩ እንደየ ተጨባጭ ሁኔታቸው የጠቅላላ ጉባኤነት መሥፈርቱ የሥራ አመራር ጉባኤው በሚኖረው የአፈጻጸም ስልት መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

**8.2. የጠቅላላ ጉባኤው መደራጀት**

8.2.1. ከላይበቊጥር4.21.1 — 4.1.17 የተዘረዘሩት በጋራብ መሆን የመንበረ ፓትርያርክ ሰንበትት/ቤቶች አንድነትን ጠቅላላ ጉባኤ ይመሠርታሉ፡፡

8.2.2. የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢየመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት  ሰንበት ት/ቤቶች  ማደራጃ መምሪያዋና ሓላፊ እና የሰ/ት/ቤቶች አንድነት ተቀዳሚ ም/ሰብሳቢ ይሆናሉ፡፡

8.2.3. ጠቅላላ ጉባኤው በቊጥር 11  / ዐሥራ አንድ / የመንበረ ፓትርያክ  ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ሥራ አመራር እና ቊጥሩ 5 / አምስት / የሆነ የአፈጻጸም ክትትል ጉባኤ ይወከላል ፡፡ይህም የማደራጃ መምሪያውን  ሓላፊ አይጨምርም ፡፡

8.2.4. የአንድ ምርጫ የሥራ ዘመን 3 /  ሦስት ዓመታት ብቻ  / ይሆናል ፡፡ ለአመራርነትም ሆነ ለአፈጻጸም ክትትል ከወረዳ ጀምሮ እስከ መንበረ ፓትርያርክ  ባለው መዋቅር ማገልገል የሚቻለው በተከታታይ ለሁለት የሥራ ዘመናት  ብቻ ይሆናል ፡፡ በሥራው እና በመልካም አፈጻጸሙ ከታመነበት በመካከል አንድ የሥራ ዘመን አልፎ በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡፡ የአጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች አደረጃጀትም በዚሁ መሠረት ተግባራዊ ከሚሆንበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡\በሁሉም የአደረጃጀት እርከኖች ለሁለተኛ ጊዜ  የሚቀጥሉት አባላት በጠቅላላ ጉባኤ ቀርበው  በመደበኛው አመራረጥ መሠረት ድምፅ ይሰጥባቸዋል፡፡

8.2.5. ለመንበረፓትርያክ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ከተመረጡት የሥራ አመራር ጉባኤው አባላት መካከልም አንድ ተቀዳሚ ምክትል ሰብሳቢ፣ አንድ ምክትል ሰብሳቢና አንድ ዋና ጸሐፊ የሚሰየም ሲሆን የተቀሩት አባላት የየማስተባበሪያው  ሓላፊዎች እና  አባላት ይሆናሉ፡፡

8.2.6. በአፈጻጸም ክትትል ጉባኤ አባላት መካከልም አንድ ሰብሳቢ ፣ አንድ ጸሐፊ የሚሰየም ሲሆን የተቀሩት የጉባኤው አባላት እና የየሥራ ዘርፉ ክትትል ሓላፊ ይሆናሉ፡፡ በዚህ የክትትል ሥራ ዘርፍ የክዋኔ ክትትል እና የሒሳብና በጀት ክትትል ሥራዎች ይደራጃሉ፡፡ በሥራቸውም ሥራውን የሚያከናውኑ አባላት ይመደቡላቸዋል፡፡

8.3. የመመረጥ መብት እና ወሰን

ሁሉም የጠቅላላ ጉባኤው አባላት በጠቅላላ ጉባኤነት በእኩል ድምፅ የመስጠት መብት ሲኖራቸው በሥራ አመራር እና በአፈጻጸም ክትትልነት ለመመረጥ የሚችሉት

8.3.1. ከአህጉረ ስብከቶች የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት አንድ የሥራ ዘመን ለመንበር ፓትርያርክ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት በቋሚነት ከተመረጡ አባላት፤

8.3.2. በተለየ ሁኔታ ከአዲስ አበባ ሀገረስብከት የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት አንድ የሥራ ዘመን ለመንበረ ፓትርያርክ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት በቋሚነት ከተመረጡ አባላት፤

8.3.3. በተለየ ሁኔታ የሥራ አመራሩ በየጊዜው እየተገናኘ መሰብሰብና መሥራት የሚችልበትን ዕድል ከመፍጠር አኳያ ሁሉም የአዲስ አበባ ሰንበት ት/ቤቶች የተወከሉና በክፍለ ከተማ ጠቅላላ ጉባኤ አባል የሆኑ አባላት

8.3.4. በአንድነቱ ጥያቄ መሠረት በአጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች የተረጋገጠላቸው አንጋፋ እና ጠንካራ የሚባሉ አገልጋይ፣ ምሁራንና ባለሙያዎች የሰንበት ት/ቤት አባላት

8.3.5. የአፈጻጸም ጥንካሬ ያላቸው ስለመሆኑ ከአንድነቱ እንዲሁም ከአጥቢያ ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የሰንበት ት/ቤት አባላት ብቻ ናቸው፡፡

9. የጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ጊዜ

በየደረጃው ያለው የሰንበት ት/ቤቶች ጠቅላላ ጉባኤ የሰብሰባ ጊዜው በዓመትሁለት ጊዜያት ሆኖ የሥራዘመኑን በየስድስት ወራት የከፈለ ይሆናል በሚለው የውስጥ ዝርዝር ማስፈጸሚያሰነድመሠረት ሆኖ ለአተገባበር በሚያመች ጊዜ ማለትም የቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሥራ በጀት ዓመትመጀመሪያ ሐምሌ 1 የሚለውን ታሳቢ በማድረግ ፡

9.1. 1ኛው ጠቅላላ ጉባኤ በሰኔ ወር የሚካሄድ ሲሆን ልዩ ልዩ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆኖ በዋናነት የዓመቱን ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እና የቀጣዩን የበጀት ዓመት የአንድ ዓመት ዕቅድ ማጽደቅ ይጠበቅበታል፡፡

9.2. 2ኛው የግማሽ ዓመት ጠቅላላ ጉባኤ ታኅሳስ ይሆናል ሲሆን ልዩ ልዩ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆኖ በዋናነት የግማሽ ዓመት አፈጻጸም ግምገማ እና የቀጣይ ትኩረት አቅጣጫዎችን ይወሰናል፡፡

10. የሥራ አመራር የሥራ ዘመን

በውስጥ ዝርዝር ማስፈጸሚያ ሰነድ ምዕራፍ አምስት አንቀጽ 5.2.5 ላይ እንደተገለጸው የአንድ ምርጫ የሥራ ዘመን 3 /ሦስት ዓመታት ብቻ/ ይሆናል፡፡ ለአመራርነትም ሆነ ለአፈጻጸም ክትትል ከወረዳ ጀምሮ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ባለው መዋቅር ማገልገል የሚቻለው በተከታታይ ለሁለት የሥራ ዘመናት ብቻ ይሆናል፡፡ በሥራው እና በመልካም አፈጻጸሙ ከታመነበት በመካከል አንድ የሥራ ዘመን አልፎ በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡፡ የሀገረ ስብከት፣ የወረዳ/ ክ/ከተማ እና የአጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች አደረጃጀትም በዚሁ መሠረት ተግባራዊ ከሚሆንበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

11. የጠቅላላ ጉባኤያት ምርጫ የሚካሄዱባቸው ጊዜያት

የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ተቋማዊ አደረጃጀት የውስጥ ዝርዝር ማስፈጸሚያ ሰነድ ምዕራፍ 2 የጠቅላላ ጉባኤው የወል ድንጋጌዎች አንቀጽ 2.2.1.1 ከአጥቢያ እስከ ሀገረ ስብከት ሰ/ት/ቤቶች አንድነት



E.O.T.C Patriarchate Head Sunday School department

ያሉ ጠቅላላ ጉባኤያት ምርጫቸው የሚያካሒዱት ከግንቦት እስከ ታኅሳስ ሆኖ የመንበረ ፓትርያርክ ሰ/ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ ምርጫ እስከ ግንቦት የሚፈጸም ይሆናል የሚለው በተናበበ መልኩ ሲተገበር በሚከተለው አግባብ ይሆናል።

11.1. የአጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች ጠቅላላ ጉባኤያት በዓመቱ ታኅሳስ እና ሰኔ ወር ላይ፤

11.2. የወረዳ / ክፍለ ከተማ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤያት በዓመት ሦስት ጊዜ ሆኖ ሃምሌ፣ ኅዳርና መጋቢት ወር ላይ፤

11.3. የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤያት ታኅሳስ እና ሰኔ ወር ላይ፤

11.4. የመንበረ ፓትርያርክ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ ጥቅምት እና ግንቦት ወይም ሰኔ በበዓለ ጰራቅሊጦስ ቀን ይሆናል።

12. **አዲሱን ማስፈጸሚያ ሰነድ አተገባበር አግባብ**

ከአጥቢያ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ሰንበት ት/ቤቶች መዋቅር ትግበራ እና የሥራ አመራር ምርጫ በተናበበ እና ወጥነት ባለው መልኩ ለመተግበር በአሁኑ ጊዜ የምንከተለው አካሄድ የተለያየ በመሆኑ በውስጥ ዝርዝር ማስፈጸሚያ ሰነዱ መሠረት ለመተግበር በሚከተለው አግባብ እንዲሆን ይጠበቃል።

12.1. ለሥራ አመራርነት የተመረጡ አባላት የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት ብቻ ነው። ነገር ግን በምርጫ ዘመናቸው ማብቂያ ወቅት ላይ በሰንበት ት/ቤቱ ውስጥ አመራር ለመቀየር የሚያስቸግሩ ከባድ ችግሮች ከተከሰ ምርጫ ማድረግ እስኪቻል ከወረዳው/ክፍለ ከተማው አንድነትና ከሀገረ ስብከቱ አንድነት በመወያየት መፍትሔ እንዲያገኙ ያደረጋል፤

12.2. አንድ የሥራ አመራር አባል ባሳለፈው ሦስት ዓመት የአገልግሎት ዘመን ውስጥ የሰጠው መልካም አገልግሎት ታይቶ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ እጩ ሆኖ በመቅረብ ሊመረጥ የሚችል ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ በተከታታይ ሊመረጥ አይችልም። ነገርግን በአገልግሎት ዘመኑ ወቅት ያደረገው አስተዋጽዖ ጠቀሜታውና አስፈላጊነቱ ከታመነበት አንድ የምርጫ ዘመን እያሳለፈ በእጩነት በመቅረብ ለመመረጥ ይችላል፤

12.3. አዲሱ ተቋማዊ አደረጃጀት መመሪያ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት የተመረጠ የሥራ አመራር አባልእና በተለየ ሁኔታ የምርጫ ዘመን ሳይደርስ በሟሟያ ምርጫ የተመረጠ የአመራር አባል የአገልግሎት ጊዜው ሁለት ዓመት እና ከዛ በላይ የሆነው አባል ሁለት ዓመቱ እንደ መጀመሪያ ሙሉ ዙር የምርጫ ጊዜ እንዳገለገለ ይቆጠራል።

12.4. አንድ እጩ አስቀድሞ የመጀመርያ ዙር ብቻ ያገለገለ ከሆነ ድጋሜ መመረጥ ይችላል። ከዚህ ምርጫ ዙር በፊት ቀድሞ ለሦስት ዓመት ካገለገለ ሁለቱን ዙር እንደጨረሰ ተቆጥሮ ምርጫ መሳተፍ አይችልም።

12.5. በሥራ አመራርነት ከሁለት ዓመት በታች የሆነው አባል በቀጣዩ ምርጫ ቀድሞ ያገለገለው ዓመት ሳይቆጠር እንደ አዲስ የመጀመርያ ዙር ተደርጎ የአገልግሎቱ ዘመኑ ታሳቢ ይደረጋል በቀጣይ ምርጫም ለሁለተኛ እጩ ሆኖ መመረጥ ይችላል።

12.6. ተመራጭ የሥራ አመራር አባላት የተጣለባቸውን ኃላፊነትና አደራ ወደጎን በመተው ከሰንበት ት/ቤቱ መመሪያና ደንብ ውጪ የሆኑ ተግባራትን ሲፈጽሙና ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ሃይማኖታችንንና ሰንበት ት/ቤቱን በሚጎዳ ተግባር ላይ ተሰማርተው ከተገኙ የሰንበት ት/ቤቱ የሥራ አመራር ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመሆን ለጠቅላላ ላጉባኤ ቀርቦ የአገልግሎት

ዘመናቸውን ሳይፈጽሙ ከሥራ አመራር አባላትነትና ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ ሊያደርግ ይችላል፤ ጠቅላላ ጉባኤው ሟሟያ ምርጫ ሊያደርግ ይችላል በሟሟያ የተመረጠው አባል እስከ ቀጣይ ሀገረ ስብከት /ሀገር አቀፍ ምርጫ ዘመን ድረስ ያለው አገልገሎት አቆጣጠር ከላይ በቁጥር 5.5. በተጠቀሰው መሠረት ይሆናል፡፡

12.7. ተመራጭ የሥራ አመራር አባል የአገልግሎት ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት በልዩልዩ ምክንያት አገልግሎቱን መቀጠል ካልቻለ ከተጠባባቂ እየተተካ አገልግሎቱ ይከናወናል፤

12.8. ከላይ በተራ ቁጥር 5.7. መሠረት በተጠባባቂነት የተመረጡት አባላት ተተክተው ከአለቁ እንዲሁም የሥራ አመራሩ አባላት በተለያየ ምክንያት ከጎደሉና የሥራ አመራሩ ቀሪ የአገልግሎት ዘመን ከአንድ ዓመት በላይ ከሆነ የሥራ አመራሩ በመስፈርቱ መሠረት በሥራ አመራር ጉባኤ አባልነት ገብተው ሊያገለግሉ ይችላሉ የሚላቸውን አባላት በመምረጥና በጠቅላላ ጉባኤ በማስጸደቅ እና ለገዳሙ ሰበካ ጉባኤና ለወረዳ/ ክፍለ ከተማ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት በማሳወቅ እንዲተካ ያደርጋል፤ተተኪው የሥራ አመራር አባል የሚያገለግለው በአገልግሎት ላይ ያለው ሥራአመራር ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡ሆኖምግን የሥራ አመራሩ ቀሪ የአገልግሎት ዘመን ሊጠናቀቅ አንድ ዓመት እና ከዚያ በታች ብቻ የቀረ ከሆነ የሥራ አመራሩ ለቀሪው የአገልግሎት ጊዜ አዲስ ተተኪ አባላትን መተካት አይችልም፡፡ ነገር ግን የጎደሉት የሥራ አመራር አባላት ከጠቅላላው 2/3ኛ እና ከዚያ በላይ ከሆኑ በሀገረ ስብከቱና በክፍለ ከተማው አንድነት በማስወሰንእንዲተካ /እንድትተካ ያደርጋል፤

12.9. በሥራ ላይ ያሉት የሥራ አመራር አባላት የሥራ ዘመን ከመጠናቀቁ በፊት ኮሚቴ አባላትን ከወረዳው/ክፍለ ከተማው አንድነት ተወካይ ጋር በመሆን ያስመርጣል፡፡ ነባሩ ሥራ አመራር የምርጫ እንቅስቃሴዎች እንዲጀመሩ በማድረግ የአገልግሎት ዘመኑ ከመጠናቀቁ ሁለት ወር በፊት የአዲስ ሥራ አመራር አባላት ምርጫ እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡አዲስ የተመረጡትም የሥራ አመራር አባላት በይፋ አገልግሎታቸውን የሚጀምሩት በአገልግሎት ላይ ያለው የሥራ አመራር ጉባኤ ምርጫው በተካሄደ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲስ ለተመረጠው ሥራ አመራር ጉባኤ ርክክብ ሲፈጸም ይሆናል፡፡

## 13. የሥራአመራር ጉባኤ አባላት የመመረጫ መሥፈርት

የሥራ አመራር ጉባኤ እጩ አባላት ሆኖ ለመመረጥ ብቁ የሚሆኑ የሰንበት ት/ቤቱ አባላት ምንም ዓይነት የፆታ ሆነ ሌላ ልዩነት ሳይኖር የሚከተሉትን መሥፈርቶች ማሟላት ይገባቸዋል፡-

13.1. በሰንበት ት/ቤቱ መደበኛ አባልነት ቢያንስ አምስት ዓመት የሞላቸው መደበኛና ልዩ መደበኛ አባል የሆኑ

13.2. ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን የማይለዩ የዳበረ የሃይማኖት ትምህርት ዕውቀት ያላቸው፤በሕገ ቤተ ክርስቲያን የጸኑ፤በመንፈሳዊ ሕይወታቸው፤ በግብረገብነታቸው፤በትህትናቸውና በአስተዋይነታቸው አርአያ የሆኑ፤

13.3. በሰንበት ትምህርት ቤቶች መዋቅራዊ መመሪያ ላይ የተቀመጠው የመመረጫ ዕድሜ የሚያሟሉሆነው ዕድሜያቸው ከ33 ዓመት በታች የሆኑ አባላት ከ40% በላይ መሆን አለባቸው፡፡

13.4. ለአገልግሎቱ በቂ ጊዜ ያላቸው፤ የመምራትና የማስተዳደር ክህሎት ያላቸው ለሰንበት ት/ቤት ብሎም ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ኹለንተናዊዕድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማድረግ ጥብዓት ያላቸው፡፡

13.5. በማናቸውም ሁኔታ መብታቸው በሕግ ያልተገደበ በሰንበት ት/ቤቱ ላይም በችግር ፈጣሪነት የማይታወቁ፤

13.6. በሰንበት ት/ቤቱ መደበኛ መርሐ ግብር ላይ በቋሚነት የሚሳተፉና ላለፉት ሦስት ዓመታት በሥራ አመራርነት ወይም በክፍላት ወይም በሌሎች የሰንበት ት/ቤቱ አገልግሎቶች ላይ ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ የሚገኙ፤

13.7. በሰንበት ት/ቤቱ እና በደብሩ የመደበኛ ተቀጣሪ አገልጋይ ያልሆኑ መሆን ይኖርባቸዋል፤ ይህ መርህ ከሰንበት ት/ቤት ማደራጃ ኃላፊ ውጪ በተዋረድ ባሉ የበላይ መዋቅሮችም ተፈጻሚ ይሆናል፤

13.8. የሰንበት ትምህርት ቤቶችን መመሪያና ደንብ አክብረው የሚያስከብሩ፤ ምሥጢር ጠባቂ የሆኑ፤

13.9. በሌላ በማንኛውም አደረጃጀት (ማኅበራት) ውስጥ በሓላፊነት የሌሉ፤ በማንኛውም ሁኔታ ቅድሚያ ለሰንበት ትምህርት ቤት የሚሰጡ።

## 14. የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት መዋቅር ተወካዮች አመራረጥ

የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ተቋማዊ አደረጃጀት የውስጥ ዝርዝር ማስፈጸሚያ ሰነድ ምዕራፍ 2 የአጥቢያ ሰንበት ት/ቤት ሥራ ማስተባበሪያዎች በአንቀጽ 2.3 ያሉ ለዩ ለዩ የሰንበት ት/ቤቱ ልዑካን በሚለው አወካከል ሂደት በሚከተለው አግባብ ይሆናል።

14.1. ተጠሪነታቸው ለሥራ አመራር ሆኖ ሰንበት ት/ቤቱን በሰበካ ጉባኤው ፣ በአጥቢያው የልማት ኮሚቴ ፣ በአጥቢያው የስብከተ ወንጌል ኮሚቴ ፣ በየደረጃው ባሉ የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ቋሚ ተወካይነት እና በመሳሰሉት የሚወከሉ አመራረጣቸው በአመራሩ የምልመላ መሥፈርት አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባኤ ዕውቅና የሚሰጣቸው ይሆናል ።

14.2. በአጥቢያው የሥራ አመራር ምርጫ ዕለትም ከአጥቢያ ሰንበት ት/ቤት የሚወከሉ የአንድነቱ ሁለት ተወካይ ማለትም የሰንበብ ት/ቤቱ ሰብሳቢ እና በአመራር ልምድ ያለው አንድ አገልጋይ በሥራ አመራሩ ዕውቅና ይሰጠዋል ተጨማሪ አገልጋዮችን ወረዳ/ክፈለ ከተማ አንድነቱ በሚጠይቀው መሠረት አጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች ይመድባሉ።

14.3. በወረዳ ቤተ ክህነቱ ሥር የሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶች የወረዳው /ክፍለ ከተማው/ ቤተ ክህነት ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ናቸው። ሁሉም ወረዳ/ክፍለ ከተማ/ ሰንበት ት/ቤቶች በአመራሮቻቸው አማካኝነት ሆኖ ከሁለቱ ተወካዮች መካከል የክፍለ ከተማው ሥራ አመራር ይመረጣል።

14.4. በመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስበከቱ ሥር የሚገኙ የወረዳ /የክፍለ ከተማ/ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ኹሉ የሀገረ ስብከቱ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ሲሆኑ ከመንበረ ጵጵስናው እና ዙርያ አጥቢያዎች ከሚወከሉ ተወካዮች እና በአጥቢያ ሰንበት ት/ቤቶች የተረጋገጠላቸው አንጋፋ እና ጠንካራ አገልጋይ፣ ምሁራንና ባለሙያዎች የሰንበት ት/ቤት አባላት ያካትታል።

14.5. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤቶች መዋቅራዊ አደረጃጀቶች ኹሉ በውክልና የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ሆነው በውስጥ ደንቡ በምዕራፍ 5 በአንቀጽ 5.3 የመመረጥ መብት እና ወሰን ከቁጥር 5.3.1 እስከ 5.3.5 በተዘረዘርው መሠረት ይሆናል።

14.6. አስመራጭ ኮሚቴዎቹም በወረዳ፣ በሀገረ ስብከት እና በመንበረ ፓትርያርክ አመራር አባላት ጊዜውን ጠብቆ የሚሰየሙ ይሆናል።

## 15. የመዋቅር ልዑካን እና ታዛቢዎች

15.1. የመዋቅር ልዑካን የምርጫ ታዛቢዎች ምርጫው በተቀመጠለት መመሪያና ሥርዓት መከናወኑን ማረጋገጥ ይሆናል።

15.2. በእነዚህ ተወካዮች የሚሰጠው ማረጋገጫ በላይኛው መዋቅር የዚህን ምርጫ ውጤት ቅቡልነት የሚወስን ይሆናል፡፡

15.3. በአጥቢያ ሰንበት ትምህርት ቤት ሥራ አመራር ምርጫ የአጥቢያ/የደብሩ ሰበካ ጉባኤ ተወካይ እና የወረዳ/የክፍለ ከተማ ተወካዮች መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

15.4. ለወረዳ/ ክፍለ ከተማ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ምርጫ የወረዳ/ክፍለ ከተማ ቤተ ክህነት እና የሀገረ ስብከቱ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ተወካይ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

15.5. ለመንበረ ጵጵስና ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ምርጫ ከሀገረ ስብከቱ እና የመንበረ ፓትርያርክ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ተወካይ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

15.6. ለመንበረ ፓትርያርክ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ምርጫ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ተወካይ መገኘት ይገባቸዋል፡፡

15.7. በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ እንደ ነባራዊ ሁኔታው ሌሎች ታዛቢዎች ሊሰየሙ ይችላሉ፡፡

**16. የአስመራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም**

**ተጠሪነቱ፡- ለየመዋቅሩ የጠቅላላ ጉባኤ ነው፡፡**

16.1. የአስመራጭ ኮሚቴ መመረጫ መሥፈርት

የሥራ አመራር አስመራጭ ኮሚቴ ሆነው የሚመረጡ አባላት ብዛታቸው አምስት ሆኖ ከአፈጻጸም አማካሪዎች ጉባኤ አንድ ተወካይ እና አራት ከመደበኛና ልዩ መደበኛ የሰንበት ት/ቤቱ አባላት ይሆናሉ፡፡ በሥራ ላይ ያለው ሥራ አመራር ጉባኤ የአገልግሎት ዘመን በሚጠናቀቅበት ዓመት ከሁለት ወር በፊት በሥራ አመራሩ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ይሆናል፡፡ በምርጫው ምንም ዓይነትየጾታ ወይም ሌላ ልዩነት ሳይኖር የሚከተሉትን መሥፈርቶች ማሟላት ይገባቸዋል፤

16.1.1. በሰንበት ት/ቤቱ መደበኛ አባልነት ቢያንስ ሦስት ዓመት የሞላቸው፤

16.1.2. በጎ አርአያነት ያለው ክርስቲያናዊ ሕይወት የተላበሱ፤

16.1.3. የሰንበት ትምህርት ቤቱንና የአባላቱን ነባራዊ ሁኔታና በሚገባ የሚረዱ፤

16.1.4. ከግለሰባዊ፤ ከስሜታውና ከቡድንተኝነት አስተሳሰብ ነጻ የሆኑ፤

16.1.5. የሰንበት ትምህርት ቤቱን ሕግና መመሪያ የሚያከብሩ ምሥጢር ጠባቂ የሆኑ፤

16.1.6. በዚህ መሥፈርት መሰረት በጠቅላላ ጉባኤው ሁለት ወር በፊት ጉባኤ ላይ ይመረጣሉ፤

16.1.7. የተመራጮች ዝርዝርና ድርሻ በየደረጃው ላሉ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት መዋቅሮች በደብዳቤ ይልካሉ፤

16.1.8. ከክፍለ ከተማ/ወረዳ በላይ ላሉ መዋቅሮች አስመራጭ ኮሚቴ ለመሆን አባላቱን የሚያውቅ፤ በሰንበት ት/ቤት አንድነት በአስመራጭነት በሚመረጥበት መወቅር በአመራርነት ወይም በክፍል አገልገሎት አባልነት ቢያንስ ከ6 ዓመት በላይ በአንድነቱ ልምድ ያለው፤

16.1.9. ከክፍለ ከተማ/ወረዳ በላይ ላሉ መዋቅሮች አስመራጭ ኮሚቴ ምርጫን በሥራ ላይ ያለው ሥራ አመራር ጉባኤ የአገልግሎት ዘመን በሚጠናቀቅበት አዲስ ምርጫ ከሚከናውንበት ጠቅላላ ጉበኤ በፊት ባለው ጠቅላላ ጉበኤ በሥራ አመራሩ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ይሆናል፡፡

16.2. አስመራጭ ኮሚቴ ተግባርና ሓላፊነት

16.2.1. አጠቃላይየምርጫሒደቱበአሠራሩመሠረትበበላይነትይመራል

16.2.2. የአስመራጭ ኮሚቴው የአገልግሎት ጊዜ ከተመረጠበት ቀን ጀምሮርክክብ እስከ ተከናወነበትድረስብቻነው

16.2.3. የምርጫውን ሒደት ዝርዝር የትግበራ ዕቅድ በማዘጋጀት ያሳውቃል፤

16.2.4. አስፈላጊውን የምርጫ ማስፈጸሚያ በጀት ከሥራ አመራሩ ጋር በመነጋገር ያስውስናል፤

16.2.5. የምርጫውን አካሄድና የመምረጫ መሥፈርት ለጠቅላላ ጉባኤ አባላት በጉባኤና በሌሎች መንገዶች ያሳውቃል

16.2.6. እጩዎችንየ ሚጠቁሙ አባላት በምርጫ ማስፈጸሚያ መመሪያው መሠረት መሥፈርቱን የሚያሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥና ቅጽ በማዘጋጀት ጥቆማ እንዲያደርጉ ያደርጋል፤

16.2.7. አባላት በመስፈርቱ መሰረት እጩዎች እንዲጠቁሙ እድል ይሰጣል፤

16.2.8. ለሥራ አመራርነት የተጠቆሙ እጩዎችን በመመዘኛ መሥፈርቱ መሠረት በመገምገም የመጨረሻ እጩ ተመራጮችን የሰንበት ት/ቤቱ መደብ የሚፈቅደውን የአመራር ብዛት ከነተጠባባቂ ከ75% እስከ 100% ተጨማሪ ዝርዝር፤ የምርጫውን ቀንና የአፈጻጸም ሂደቱን ለሰንበት ት/ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ በማሳወቅ እጩዎቹን ለግምገማ ያቀርባል፤

16.2.9. በጠቅላላ ጉበኤ ተገምግመው ያለፉትን እጩዎች ከምርጫው ዕለት በፊት የእጩዎች ስመ ክርስትና በደብራቸው ወይም በሌላ ገዳማት ወይም አድባራት በትንሹ ለአንድ ሱባኤ ጸሎት እጣን እንዲደርስላቸው ያደርጋል፤

16.2.10. የምርጫው እጣ ሲወጣ አመራር መመርያውን መሰረት አድርጎ በሚወስነው እንደ ሰንበት ት/ቤቱ የእድሜ/ልምድ/ ተዋጽኦ መቶኛ መጠን መሰረት ከ33 በታች እና በላይ በተናጥል ለየብቻ እጣ የማውጣት ሥነ ሥርዓት ይከናወናል ፤

16.2.11. ምርጫው ተከናወነበት ወቅት ጀምሮ እስከ ርክክብ እስከ. ፈጸም ድረስ በቀድሞው የሥራ አመራር ጉባኤእና በአዲሱ ተመራጭ የሥራ አመራር መካከል የልምድ ልውውጥ እንዲፈጸም ሁኔታዎችን በማመቻቸት በጋራ እንዲሠሩ ያደርጋል፤

16.2.12. የአፈጻጸም ክትትል እና ቁጥጥር ጉባኤ አባላት ሊሆኑ የሚችሉ አባላትን ይመለምላል፤

16.2.13. የአፈጻጸም ክትትልጉባኤ አባልነት የመለመላቸውን እጩአባላት ለጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ ያስመርጣል፤

16.2.14. ለሥራ አመራር እና የአፈጻጸም ክትትል እና ቁጥጥር ጉበኤ እጩ አባላት ብዛት ሰንበት ት/ቤቱ በተመደበው ደረጃ መሠረት ሆኖ ከአመራሩ ብዛት 75% እስከ 100% ተጨማሪ በተጠባባቂነት ያስመርጣል፤

16.2.15. የምርጫውም ሒደት ግልጽ፣ ታማኝነት ያለው፣ ለሁሉም አባላት መረጃ እንዲደርስ በማድረግ በሰነድ የተደገፈ እንዲሁም ምቹ በሆነ ቦታና ሁኔታ ታዛቢዎች ባሉበት እንዲከናወን ያደርጋል፤

16.2.16. የምርጫ ሒደትን በተመለከተ በሥራ አመራር ጉባኤ አባላት ምርጫ ዕለት የምርጫው ድምፅ አሰጣጥ ከመጀመሩ አስቀድሞ በአስመጭ ኮሚቴ አማካኝነት መራጮች በእጩነት ስለቀረቡት አባላት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና የተጠቆሙ እጩ አባላትን ማንነት በትክክል እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም በቀረቡት እጩዎች ላይ ጠቅላላ ጉባኤው ተቃውሞ ካለው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት 51% በላይ ከሆነ ይቀበላል ያልተካተቱ ዕጩዎች ካሉ እንዲካተቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ዕድል ይሰጣል፡፡

16.3. በምርጫ ሂደት ስለሚደረገ የጸሎት ሥርዓት

16.3.1. ምርጫው ዕለት በፊት በጠቅላላ ጉባኤ በግምገማ ያለፉ የእጩዎች ስመ ክርስትና በደብራቸው ወይም በሌላ ገዳማት ወይም አድባራት በትንሹ ለአንድ ሱበኤ ጸሎት እጣን እንዲደርስላቸውያደርጋል፡፡

16.3.2. በምርጫው ዕለት የድምፅ አሰጣጥ በፊት ወንጌል በማድረግ የምርጫ ዕጣ አወጣጥ ሥርዓቱ ይከናወናል፡፡



E.O.T.C Patriarchate Head Office Sunday School department

16.3.3. የአመራረጥ ሥርዐቱ በዕጣ የሚፈጸም ሆኖ ልዩ ነገር ከገጠመ በሰንበት ት/ቤት የውስጥ አሠራር መሠረት ምርጫው ይካሄዳል፡፡

16.4. **የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት**

16.4.1. ምርጫው በዕጣ ሲፈጸም የጋራ ጸሎት ከተከናወነ በኋላ አስመራጭ ኮሚቴው በሚያዘጋጃቸው አባቶች ወይም የሰንበት ትምህርት ቤቱ አባላት ወይም እንግዶች ዕጣው ይወጣል፡፡

16.4.2. የዕጣው አወጣጥ ርቱዕ እንዲሆን የሚዘጋጁት ዕጣዎች በሙሉ እኩል መጠን እና ተመሳሳይ ቅርጽ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

16.4.3. አስቀድመው የሚወጡ ዕጣዎች የሥራ አመራር አባላት ይሆናሉ፤ ቀሪዎቹ በቅደም ተከተል ተጠባባቂዎች ይሆናሉ፡፡

16.4.4. ዕጣዎቹ ወጥተው ከተጠናቀቁ በኋላ የሁሉም እጩዎች ሳይጓደል በዕጣ ተካተው እንደነበረ ዕጣዎችን በሙሉ በመግለጥ ለጉባኤው እንዲታይ ይደረጋል፡፡

16.5. የተመራጮች ሥራ ድልድል እና ቃለ መሐላ

16.5.1. ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ የሥራ አመራር ጉባኤ እና አፈጻጸም ክትትል አባላት እና ተጠባባቂዎች በአንድነት በመቆም በጠቅላላ ጉባኤው ፊት ቃለ መሐላ ይፈጽማሉ፡፡

16.5.2. የሥራ አመራር ጉባኤ አባላት የሥራ ድልድል የሚከናወነው አዲሱ ሥራ አመራር፣ አስመራጭ ኮሚቴ በመሆን የተመራጮቹን የዕውቀት፣ የልምድ፣ የክህሎት አቅምና ፍላጎት መሠረት በማድረግ በስምምነት ይከናወናል፡፡ ክርክሮች ቢኖሩ አዲስ ተመራጭ የአመራር አባላት ይመራናል ብለው ያመኑበትን አባል በድምጽ ብልጫ ሰብሳቢ ምክትል ሰብሳቢ እና ጸሐፊወን ይሰይማሉ፡፡

16.5.3. የሥራ አመራር ጉባኤ ጽ/ቤት አባላት የሥራ ድልድል የሚከናወነው አዲሱ ሥራ አመራር፣ ከአስመራጭ ኮሚቴ ጋር በመሆን የተመራጮቹን የዕውቀት፣ የልምድ፣ የክህሎት አቅምና ፍላጎት መሠረት በማድረግ በተመራጩ አመራሩ ስምምነት ይከናወናል፡፡ በእለቱ የጽህፈት ቤት አባላት ድልድል ለጠቅላላ ጉበኤው ይገለጣል፡፡

16.5.4. አባላት ጥቆማ ለአስመራጭ ኮሚቴው ይሰጣሉ፡፡ አስመራጭ ኮሚቴ የሚጠቀሙበት ምቹ ሥርዓት ይዘረጋሉ

16.5.5. የከጽ/ቤት ውጪ ያሉ የአመራር አባላት የሥራ ድልድሉ ምርጫው ከተከናወነ ከኹለት ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ በአመራር ጉባኤው ይከናወናል፡፡

16.6. ምርጫ በተመለከተ የሚነሱ ቅሬታዎች

በምርጫ ዙሪያ የሚነሡ አፈጻጸም ቅሬታዎች በመጀመሪያ በአስመራጭ ኮሚቴ መፍትሔ እንዲያገኝ ይደረጋል፤ ነገር ግን በአስመራጭ ኮሚቴው መፍትሔ ማግኘት የማይችል ከሆነ እንደ ቅሬታው አይነት በጠቅላላ ጉበኤ በሰበካ ጉበኤወይም በወረዳ/ክፍለ ከተማ መንበረ ጵጵስና ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት መፍትሔ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ጠቅላላ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል፡፡

16.7. በየደረጃው ያለው የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የሥራ አመራር አመራረጥ

በአጥቢያ አፈጻጸም ተመሳሳይ መልኩ ቀጣይ መዋቅራትም ከላይ በተቀመጠው አግባብ ለወረዳ/ክፍለከተማ ፤ለመንበረ ጵጵስ እና ለመንበረ ፓትርያሪክ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት አመራር ምርጫ ይፈጽማሉ ፡፡ ከወረዳ /ክፍለ ከተማ መዋቅር ጀምር በተዋረድ እስከ መንበረ ፓትርያሪክ የጠቅላላ ጉበኤው አባላት የአጥቢያ/ክፍለ ከተማ/መንበረ ጵጵስና ተወካዮች በመሆናቸው የአመራር ተዋጽኦ እንደሚከተለው ይሆናል

16.7.1. ለክፍለከተማ/ወረዳ/ ሰንበት ት/ቤት አንድነት የአመራር ተመራጮች ተዋጽኦ ከኢጥቢያ ሰንበት ት/ቤት ከሰንበት ት/ቤቱ ሰብሳቢ ጋር ልምድ ያላቸው በሰንበት ት/ቤቱ የአንድነት ልዑክ ሆነው ከተላኩ አባላት እና በክፍል ከተማው በአመራርነት ልምድ ካላቸው አባላት እንዲሁም በችሎታ እና ልምድን መሠረት አድርጎ ጠቅላላ ጉበኤ ላይ እንዲሳተፉ ከተጋበዙ የሰንበት ት/ቤት አባላት መሀከል ይሆናል፡፡

16.7.2. ለመንበረ ጵጵስና ሰንበት ት/ቤት አንድነት የአመራር ተመራጮች ተዋጽኦ ከክፍለ ከተማ /ወረዳ ለአመራር እጩነት የሚቀርቡ እና በመንበረ ጵጵስና አንድነትን በአመራርነት ልምድ ካላቸው እንዲሁም ከሀገረ ስብከቱ ሰንበት ት/ቤቶች በአመራርነት ችሎታ እና ልምድን መሠረት አድርጎ ጠቅላላ ጉበኤ ላይ እንዲሳተፉ ከተጋበዙ የሰንበት ት/ቤት አባላት መሐከል ይሆናል፡፡ የአመራር ተዋጽኦውም የተጀመሩ ሥራዎችን እና የአንድንቱን እሴት ቀጣይነት ለመጠበቅ በመንበረ ጵጵስናው በየትኛውም ዘመን አንድ ሙሉ የአመራርነት ዘመን እና ከዛ በላይ ከመሩ ቀደምት አመራሮች ከ30በመቶ በላይ በአመራር ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡ የሀገረ ስብከቱ ወረዳዎች የተራራቁ ከሆን የክፍለ ከተማ/ወረዳ ውክልናን ሳይጠብቅ ከመንበረ ጵጵስናው ወረደ ወይም የቅርብ ወረዳዎች እጩዎችን በአመራርነት ሊያስመርጥ ይችላል፡፡ አስመራጭ ኮሚቴው እጩዎችን ከመንበረ ጵጵስና የሰንበት ት/ቤት አንድነት አመራሮች እና ቅርበት ኖሯቸው ተወካይ እጩ ከሚያቀርቡ ከክፍለ ከተማ/ወርዳ አመራሮች ጋር በመወያየት እጩዎችን ለጠቅላላ ጉበኤ ያቀርባል፡፡

16.7.3. ለመንበረ ፓትርያሪክ ሰንበት ት/ቤት አንድነት የአመራር ተመራጮች ተዋጽኦ ከመንበረ ጵጵስና ለአመራር እጩነት የሚቀርቡ እና በመንበረ ፓትርያሪክ ሰንበት ት/ቤት አንድነትን በአመራርነት ልምድ ካላቸው እንዲሁም ከሀገረ ስብከቱ ሰንበት ት/ቤቶች በአመራርነት ችሎታ እና ልምድን መሠረት አድርጎ ጠቅላላ ጉበኤ ላይ እንዲሳተፉ ከተጋበዙ የሰንበት ት/ቤት አባላት መሐከል ይሆናል፡፡ የአመራር ተዋጽኦውም የተጀመሩ ሥራዎችን እና የአንድንቱን እሴት ቀጣይነት ለመጠበቅ በመንበረ ፓትርያሪክ በየትኛውም ዘመን አንድ ሙሉ የአመራርነት ዘመን እና ከዛ በላይ ከመሩ ቀደምት አመራሮች ከ30በመቶ በላይ በአመራር ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡ ለአሥራር አመቺነት አመራሮች በቅርበት እየተገናኙ ሥራን ለመምራት እንዲያስችል ለመንበረ ፓትርያሪክ እጩዎች ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ከሚገኙ ሰንበት ት/ቤት አባላት መሐል አስመራጭ ኮሚቴው የሀገረ ስብከቱ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት እና ከመንበረ ፓትርያሪክ ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት አመራር ጋር በመወያት እጩዎችን ያቀርባል፡፡

16.7.4. በኮሚቴው የተለዩ እጩዎች ከምርጫው ዕለት በፊት የእጩዎች ስመ ክርስትና በገዳማት ወይም አድባራት በትንሹ ለአንድ ሱባኤ ጸሎት እጣን እንዲደርስላቸው ያደርጋል፡፡

16.7.5. የምርጫው እጣ ሲወጣ የመዋቅሩ አመራር መመርያውን መሠረት አድርጎ በሚወስነው ተዋጽኦ መቶኛ መጠን መሰረት ልምድ ያላቸው እና አዲስ ወይም ከአንድ የአመራር ዘመን በታች ያገለገሉ እጩ አመራሮች በተናጥል ለየብቻ እጣ የማውጣት ሥነሥርዓት ይከናወናል::

16.8. ምርጫን ስለማሳወቅ

16.8.1. ምርጫው በተከናወነ ዕለት አስመራጭ ኮሚቴው ለጠቅላላ ጉባኤው የተመራጮችን ውጤት ፤ የሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ጸሐፊ ለጉበኤው ያሳውቃል፡፡

16.8.2. በውጤቱ መሠረት የሥራ ድልድል ከተደረገ በኋላ በአስመራጭ ኮሚቴው አማካኝነት ድልድሉ ይፋ ይደረጋል፡፡

16.8.3. በጠቅላላ ጉባኤው ፊት የተመራጮችን የተወዳዳሪዎችን ዝርዝርአጠቃላይ የምርጫው ሒደትን የምርጫውን ውጤት እና የሥራ ድልድሉን የያዘ ቃለ ጉባኤ በአስመራጭ ኮሚቴ ተዘጋጅቶና

ተፈርሞ ለገዳማት እና አድባራቱ ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤትና ለክፍለ ከተማው የሰንበት ት/ቤት አንድነት በአስመራጭ ኮሚቴው ቃለ ጉባኤ አዘጋጅነት በነባሩሥራአመራርፎርማ በደብዳቤ እንዲገባይደረጋል፤

16.8.4. ከወረዳ/ክፍለ ከተማ ጀምሮ ወደላይ ላሉ መዋቅር አንድነት የምርጫ ሪፖርት ፡፡ በጠቅላላ ጉባኤው ፊት የተመራጮችንና የተጠባባቂዎችን ዝርዝር አጠቃላይ የምርጫው ሒደትን የምርጫውን ውጤት እና የሥራ ድልድል የሚገልጽ ቃለ ጉባኤ በአስመራጭ ኮሚቴ ተዘጋጅቶና ተፈርሞ ከክፍለ ከተማ /ወረዳ ጀምሮ ላሉ መዋቅሮች የቅርብ ተጠሪ ለሆኑለት የቤተክህነት መዋቅር እና ለበላይ የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት መዋቅር በአስመራጭ ኮሚቴው ቃለ ጉባኤ አዘጋጅነት በነባሩ ሥራ አመራር ፎርማ በደብዳቤ እንዲገባ ይደረጋል፤

## 17. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

17.1. በውጭ ሀገር የሚገኙ ሰንበት ት/ቤቶች ይህን ማስፈጸሚያ ሰነድ የሚጠቀሙ ሲሆን በልዩ ሁኔታ አባላት በተለያየ አማራጭ የሚገናኙበት የቨርችዋል አሠራሮችን በሀገረ ስብከቱ ተጠንቶ ሲቀርብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

17.2. ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው አዳዲስና በመደራጀት ላይ የሚገኙ ሰንበት ት/ቤቶች ለወረዳ/ ክፍለ ከተማ ቤተ ክህነቱ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት የውስጥ አማራጭ አቅጣጫ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

17.3. በዚህም መሠረት በ2017 ዓ.ም 13ኛው ዓለም አቀፍ የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ሁሉም መዋቅር በተናበበ መልኩ መዋቅሩን እና አመራሩን አስመርጦ ለመተግበር እንዲረዳው ቀድሞ ስልጠና እና ልምምድ በማድረግ ከግንቦት 2018 ዓ.ም ጀምሮ ከላይ ከ1ኛ እስከ 4ኛ በተቀመጠው የመዋቅራት እርከን መሠረት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በየሦስት ዓመቱ በተናበበ መልኩ ወጥ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ አዲስ የሚመሠረቱና በመሐል በሚፈጠር ክፍተት ምርጫ ለማከናወን የሚገደዱሰንበት ት/ቤቶች ሁሉ በጊዜያዊነት አገልግሎቱን የሚያስጀምሩ/የሚያስቀጥሉ ጊዜያዊ አመራር አባላትን በመሰየምቆይተውይህንኑ ጊዜ እኩል አድርገው የሚፈጽሙ ይሆናል፡፡